ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 10 ቁጥር 2 የካቲት 04 ቀን 2015 ዓ.ም.

# ከፍተኛ 15 (ካዛንችስ/ባንቢስ) አድማ ግድያ 45ኛ ሙት ዓመት መታሰቢያ

**በድምጽ ለማድመጥ እዚህ ይጠቁሙ (www.yatewlid.org/images/mp3/H15Adma.mp3)**

**ዛሬ ቅዳሜ የካቲት 4 ቀን 2015 ዓ.ም. ነው። ልክ የዛሬ 45 ዓመት ቀኑ የካቲት 4 ቀን የዋለው ቅዳሜ ነበር። ይህ ቀን ለእኛ በተለይ በደርግ ቀይ ሽብር ዘመን ከፍተኛ 15 እስር ቤት ለነበርነው እጅግ መሪር ትዝታ አለው። ቀኑን እንደያ ትውልድ ወገንተኛነታችን ማሰብና ነፍስ ይማር ማለት እንገደዳለን። ሁኔታው በአቶ ነሲቡ ስብሐት መስከረም 2007 ዓ.ም. ተጽፎ ለንባብ ከበቃው "ፍጹም ነው እምነቱ ቀይ ሽብር የከፍተኛ 15 እውነተኛ ታሪክ" ገጽ 227 "2.14 የከፍተኛ 15 አድማ ተብሎ ግድያ" በሚል ርዕስ ሥር የቀረበውን ከነድምጽ ቅጂው ለማስታወስና ሰማዕታቱን ለመዘከር አቅርበንላችኋል።**

### *2.14 . የከፍተኛ 15 አድማ ተብሎ ግድያ*

**በድምጽ ለማድመጥ እዚህ ይጠቁሙ (www.yatewlid.org/images/mp3/H15Adma.mp3)**

እነ ከፈለኝ ዓለሙ ከጊዜ ወደ ጊዜ በግርፉ፣ በማሰቃየቱ በግድያው እየተደሰቱ እየተዝናኑ ይመጡ ጀመር። የሰው ስጋ በልተው ደም ጠጥተው ሲጠግቡ ሌላም ያምራቸው ጀመር። ማታም ሆነ ቀን አንዱ ሲጠራ ተገርፎ ሲመለስ ሌላ ሲጠራ ስሙን የሰማ በፍጥነት “አቤት” ብሎ በሮ ሄዶ በሽክም ይመለሳል።

ቆየት እያለ ወደ ማታ የሚጠራው የሚሰማው የሴት ስም ብቻ ሆነ። ተጠርታ የሄደችው ስትመለስ ቁንጥጫም የቀመሰች አትመስል። እነኚኛዎቹ በረው ሄደው አቀርቅረው ይመለሳሉ። ስሜታቸው ተገሎ ይላካሉ። ከዱላ የባሰ ስቃይ። አይ ሰውነት ያሰኛል። ጉልበታችንን፣ አቅማችንን፣ ስብእናችንን፣ ሁለመናችንን ወስደውታል። የነሱን የወሲብ ፍላጎት፣ እንስሳዊ ባህሪ፣ ጭካኔና ግፍ ከማስተናገድ ሌላ ምንም ምርጫ የለም። አንዳንዶች “የተስማማቸውም” የገራፊዎቹ አዝናኝ ሆነው መጠራትም አይጠበቅባቸውም።

መስተዋትም ተራዋን ያማራትን “ውይ ይሽን ቆንጆዬ ተዉት” እያለች ማስፈታት ጀመረች። እሷም በተራዋ ጭር ሲልላት አድፍጣ ለውስጥ ጉዳይ ምርመራ ትጠራ ጀመር፡፡ ዘመነ እርግማን?

በእሥር ቤቱ ግድያው እንደቀጠለ ነው። ሁሉ ነገር ተስፋ አስቆራጭ ከመሆኑ በላይ አብዛኛው ሞትን ነው የሚጠብቀው። ስለ ሞት መጨነቁን ትቶ ሁሉም ይስቃል፣ ይጫወታል፣ ያወራል፣ ይኮምካል። ቀን ሲያጫወትና ሲያስቅ የነበረ ማታ ተገድሏል። እጣው ለማንም ሊደርስ ስለሚችል የሚሆነውን መጠበቅ የከበደውም የለ። ግድያው ላይቀር የየቀን ስቃዩ፣ እየተጠሩ ግርፉ፣ ልብስ ዘረፋው፣ ምግብ፣ ስኳርና እንጨት ንጥቂያው ሁሉም መሮታል። ያጉረመርማል።

ዋናዎቹ የቀይ ሽብር ኮሚቴ አባላት በግቢው ውስጥ ከሌሉ እንደ አስናቀ ዓይነቱ አረመኔዎች የደበቀውንና አብረው የሠሩትን ሌሎች ተይዘው የመጡ ያወጡብኛል ከሚል ስጋት እየጠራ ምርመራ ክፍል ውስጥ ያሰቃያል። ወንድወሰን ገ/ማርያምን ከመገደሉ በፊት ምርመራ ክፍል አስገብቶ እየገረፈና ብልቱን እያሸ ያሰቃየዋል፤ እዚያው አዳክሞ ሊገለው ፈልጓል። በዚህ

ላይ ጀግናው ወንድወሰን ግራ እጁን በጥይት ተመቷል። በዚህ ማሰቃየት ላይ ሳያስበው የቀይ ሽብሩ በላይ ሳሙኤል ድንገት ይደርስበታል። በተንተባተበ አነጋገሩ፤
“ምን…ምን..ምን እያደረግህ ነው?” ይለዋል።
“ያላወጣው ጉዳይ እንዳለ እየመረመርኩት ነው” ይለዋል።
በላይ ተናዶ “አንተን ማን ይህን ስልጣን ሰጠህ?” ብሎ አበሻቅጦ ያስወጣዋል።
ለጊዜው ቢሸማቀቅም ምንም አልሆነም፤ ወንድወሰንም በቀጣዩ ቅዳሜ ከሌሎች ጋር ተገደለ።

መስታዋት የሴቶች እስረኞች የውስጥ አልባሳት ሳይቀር ጫማቸውን ጭምር መዝረፍና መልበስ ብዙዎችን አስመርሯል። ከዚህ በተጨማሪም በየክፍሉ እየዞረች እንደመፈክር “ስኳር በተግባር!” እያለች ንጥቂያ ይዛለች።

አጋሰሶቹ ደምሴ፣ ሱራፌልና ሰለሞን የሚፈልጉት ክፍል ገብተው የፈለጉትን ምግብ በልተውና ከመጣው ፔርሙስ ሻዩንም፣ ቡናውንም፣ ወተቱንም ጠጥተው የደህና ቤተሰብ ልጅ ነው ያሉትን ጠርተው ለመቃሚያቸውና ለማታ ጨብሲ ብር ይጠይቃሉ። ተጠያቂው ድንገት ከሌለው ተገርፎ “ቤተሰብ ሲመጣ ያስፈልገኛልና አምጡልኝ በል” ተብሎ በቀጣዩ ቀን ይሰጣል። በዚህም አያበቁ የእሥረኛውን ምግብ በልተው፣ ቡናቸውን ጠጥተው፣ ያለውን ፍራፍሬ ሰልቅጥው፣ ሲጃራ ነጥቀው አጭሰው፣ ወደ በርጫ ከመሄዳቸው በፊት መግረፊያ ጉማሬአቸውን ይዘው በጠገበ ጉልበታቸው ደስ ያላቸውን እዛው ክፍል ውስጥ ወይም አስወጥተው ይገርፋሉ።

ከበርጫ በኋላም ጨብሰው ወደ ምርመራ ክፍል ማንም እንዳይሄድ እንቅስቃሴ እንዳይኖር ትዕዛዝ ይሰጡና የፈለጓትን ሴት ያስጠራሉ። አቆይተው ይመልሳሉ። ሁሉም አንጀቱ እያረረና እያዘነ በተለያየ መልኩ የግፈኞች መጫወቻና ስሜት ማርኪያ ይሆናሉ። ለርካሽ ተግባራቸው ተባባሪና አጫፋሪ ብሎም ገራፊ ሴቶችም አላጡም።

እንደ ግርማ ሚሊሽያ ያለ ወሮበላ ባለጌ ምርመራ ክፍል ቪላ አዳራሽ ውስጥ ከተቀመጡት በርካታ እስረኞች የፈለገውን ምርመራ ክፍል ውስጥ እያስገባ የሚደፍር ባለጌ ዱርዬ የበርካታ እህቶቻችንን ጎሊና ሰብሯል። ምንም የማድረግ አቅም የሌላቸውን ወንድሞቻቸውን አስተክዟል። በዚህ ድርጊት ወንድ ሚባል አስጠልቷቸው እስከዛሬም ብቻቸውን የተቀመጡ ቤቱ ይቁጠራቸው።

የእነዚህ ሁሉ ተደጋጋሚ የየቀን ሂደት፣ የዕለት ተዕለት ማቆሚያ ያጣ ግፍ “ምን ይመጣል ከሞት በላይ?” ከሚል እልህ ውስጥ የእስረኛው ስሜት ገብቷል። አንዳንዱ ስኳሩን ትራስ እያደረገ መደበቅ ይዟል። ማጉረምረም ተጀምሯል።

ቅዳሜ የካቲት 4 ቀን 1970 ዓ.ም. ቀኑን እስረኛው ሁሉ ደጅ ለስብሰባ ይወጣል። ዋና ዋናዎቹ የቀይ ሽብር ገዳዮች የሉም። ስብሰባው ከእስረኛው ስለሚወሰደው ምግብ፣ ስኳር፣ ልብስ ወዘተ ዝርፊያ ጉዳይ ነው። በተለይ በስኳድ ክፍል ያሉት ከሞት እንደማያመልጡ ስለሚያውቁት ምርር ባለ መልኩ የሚደረገውን ዘረፋ እያወገዙ ተናገሩ።

“ከእንግዲህ ቤተሰብም አቅሙ ተሟጧል የሚመጣውም ምግብ እያነሰ በመምጣቱ ለእኛም በቂ አይደለምና አናዘርፍም” የሚል ድምዳሜ ላይ ተደረሰ። አብዛኛው ቁጭ ብሎ ጐኑ ካለው ጋር እየተንሾካሾከ ስብሰባውን ይከታተላል። እነ ሱራፌል ብቅ እያሉ ያደምጣሉ። በዚህ ሁኔታ ቀኑ እንዳለፈ ወደ ማታ ከምርመራ ክፍል ጥሪ ተጀመረ። የተወሰነ ሰው ይጠራል ተገርፎና ተደብድቦ ይመለሳል። ሌላ ይቀጥላል። ግቢው የስም ጥሪ ብቻ ሆነ። አንዳንዴም እስረኛው ክፍል እየገቡ ከዚህ ጀምሮ ተነሱ እያሉ ማስነሳት ወይም አንተ አንተ ተነስ እያሉ ይወስዳሉ። መተራመስ ሆነ ቀኑም ጨለምለም እያለ መጣ። ብቻ አንዱ ይሄዳል ሌላው ይመለሳል። ማን ለምን እንደሚጠራ፣ ለምን እንደሚደበደብ ግራ ገብቶታል፤ በዚህ ሁኔታ ሁካታው ቀጠለ።

ወደ ምርመራው ክፍል ተጠርተው በሕይወት ከተረፉት ውስጥ ከ36 ዓመት በኋላ ለመጽሐፉ ደራሲ የሰጡት ምስክርነት እነሆ፡-

**<u>የከፍተኛ 15 ቀበሌ 32ቱ ክበበው ይርዳው</u>** *“የካቲት 4 ቀን 1970 ዓ.ም. አድማ ወይም ሤራ በሚል ሰበብ በከፍተኛ 15 የተደረገውን መጥፎ አሰቃቂ ታሪክ ትዝ ይለኛል። ቀኑ ቅዳሜ ይመስለኛል ቀበሌ 33 ይሁን አንድ ቀበሌ ውስጥ ትልቅ ዝግጅት እንደነበረ ሰምተናል። በዚያን ዕለት ልክ ወደ 10 ሰዓት ተኩል አካባቢ ላይ ሲሆን የተለመደ አንድ አባባል አለ አሰሳ ወይም ስኳርና እንጨት ከእስረኛው ክፍል እየተለቀመ ጫት ለሚቅሙ ገራፊዎቹ ወይም አብዮታውያን ነን ለሚሉ ሰዎች ሻይ*

*የሚፈላበት ይወሰዳል። እስረኛው በስኳርና እንጨት ዘረፋው በጣም ስለተማረሩ ስኳራቸውን እመኝታቸው ትራስ እየደበቁ ያስቀምጡ ነበር።*

*‘ይህንን ዝርፊያ የሚያካሂዱት መስተዋት እና ደምሴ ከእስረኛው ደግሞ ምግብ ከቤተሰብ እየተቀበሉ ለእሥረኛው የሚያከፋፍሉ አመላላሾች (እስኩፐኒ የሚባሉ) በጋራ ነው።*

*‘እስረኛው በዚህ የዕለት ተለት ዘረፋ በመማረሩ እንጨትና ስኳር መደበቁን ስለተረዱ እየዞሩ እስረኛውን እየገረፉ ስኳሩን ለመውሰድ ቢጥሩም እስረኛው ሊተባበራቸው አልቻለም። በዚህ ምክንያት እስረኛውን አንድ ባንድ እየጠሩና እየወሰዱ የመሰላቸውን እየገረፉ መመለስ ይጀምራሉ። አንዱ ተገርፎ ይመጣል ሌላው ሊገረፍ ይጠራል። ግቢው ውስጥ ትርምስ ሆነ።*

*‘እነ መስተዋት ደስ ያላቸው ጊዜ እሥረኛውን ‘ዛሬ ደብሯቸዋልና እናማሙቃቸው’ የሚል ፈሊጥ አላቸው። እሥረኛው የሚሟሟቀው በግርፍ ነው። የዚህ ዕለት መስተዋት ‘እናማሙቃቸው’ እያለች ስትገርፍ ነበር። ወደ ምርመራው ክፍል በገፍ እየወሰዱ መደብደብ ጀምረዋል። ማንም ምክንያቱን አያውቀውም ከዚህ ጀምሮ ተነስ ሲባል መክተልተል ነው።*

*‘ከከፍተኛ 15 ቀበሌ 32 በብዛት የመጡ እስረኞች አዳራሹ ውስጥ ሙልት እንዳሉ ናቸው።*

*‘ቀኑ በጣም ሰቆቃ የነበረበትና ደባሪ እንደነበረ ትዝ ይለኛል። አሁን ከምሽቱ አንድ ሰዓት እስከ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ ከሩቁ የእኔ ስም እየተጠራ ይሰማኛል። ጥሪው እየቀረበ እየቀረበ ሲመጣ ዝም ብዬ መቅረት ፈልጌ ነበረ ግን መጨረሻ ላይ ቁጥር አምስት በረንዳው ላይ ቆሞ ደምሴ ገራፊው በከባድ ድምጽ ስሜን ስለጠራ እንደማይለቁኝ ስላወኩኝ ያው ለብ ለብ ተደርጎ ለመመለስ ወደዚያ ስሄድ ልክ በረንዳው ላይ ስደርስ “መጣህ?” ብሎ ሲናገር እሰማለሁ። ምክንያቱም በተደጋጋሚ ሲጠራ ስለነበረ ነው።*

*‘አሁን በዚያ ሰዓት “ሂድ!” ብሎ ወደ ምርመራ ክፍል ሲወስደኝ ፀጉ ተገርፎ ሲመለስ ተገናኘንና “ማን ነው የጠራኝ?” ብዬ ስጠይቀው*
*“አንተን የጠራህ አስናቀ ነው” የሚል መልስ ሰጠኝ።*

*‘በዚያ ሰዓት ምርመራ ክፍል ውስጥ የሞላውን እስረኛ አቋርጬ ወደ ምርመራ ክፍሏ ልገባ ስል ጨለም ያለች ቦታ አለች። ወደ ምርመራ ክፍሉ መግቢያ ላይ ያለች ጭልምልም ትላለች። ወደዚያች ክፍል ስገባ ጥግ ጥግ ይዘው የሚጠባበቁት እነ መስተዋት እንደ ካራቲስት በዱላ፣ በካልቾ፣ በቦክስ፣ በጥፊ ያጣድፉኝ ጀመር።*

*‘እነሱ ሲደበድቡኝ ተገርሜ ዝም ብዬ እደበደብላቸው ነበር። የገባኝ በኋላ ሌሎች ሲደበደቡ ነው። ድብደባው ቀላል ባይባልም ለመገላገል ከተፈለገ ቶሎ ብሎ እንደተጎዳና እንደተሸነፈ ሰው መውደቅና ጥቅልል ብሎ መንፈራገጥና መወራጨት ባለማድረጌ እየተቀባበሉ ደበደቡኝ።*

*‘መጀመሪያ ግርፉን ሲጀምሩ የተገረፉት እስከ ልብሳቸው ሞቅ ሞቅ እየተደረገ ነበር የሚመለሱት። እኛን ግን ወደ ምርመራ ክፍል ከአስገቡ በኋላ ‘ልብሳችሁን አውልቁ’ ተባለ ሙሉ ልብሳችንን አወለቅን። በፓንት ብቻ ሆነን ዱላው ቀጠለ። ቢያንስ ወደ ሃያና ሰላሳ ወጣቶች እንሆናለን። እየተገረፍን እያለን የቀይ ሽብር ኮሚቴ አባሉ ከተማ ይመጣና ክፍሉ ውስጥ አለችው ሶፋ ላይ ይቀመጣል። ከተማ እነ መስተዋት፣ ጃምቦ፣ ሻንቄ፣ አስናቀ፣ ደምሴ እየገረፉን ዝም ብሎ ይታዘባቸዋል። ግርግሩም ስለበዛበት ይመስላል ጫት ቅሞ እንደመረቀነ ሰው ቁጭ ያለበት ዱላው ሲወርድብን ያያል።*

*‘በዚህ ሁኔታ እያለን የምርመራው ክፍል ዋናው ገዳይ ከፈለኝ ትዝ ይለኛል ጥቁር ሱሪ በነጭ ሸሚዝ እንደለበሰ በሩን በርግዶ ገባ። በዚያን ሰዓት ኢሕአፓ ተብሎ የታሰረውን የ32 ቀበሌ አብዮት ጠባቂ ግዛው ማዕከል ላይ አስተኝተውት እየደበደቡት ነበረ። ሌሎቻችን ዙሪያውን የምርመራ ክፍሉን ግድግዳ ተደግፈን ቆመናል። ምርመራው ክፍል ውስጥ ካለነው ግማሹ ልብሱን እንደለበሰ ሌሎቻችን ደግሞ በፓንት ብቻ ነበርን።*

*‘ከፈለኝ እንደገባ ማዕከሉ ላይ አለችው ጠረጴዛ ላይ ተንደርድሮ ቁጭ አለ።*
*ወዲያው ግርግሩን አየና ‘ምንድነው? ምን እየሠራችሁ ነው?’ ብሎ እነመስተዋትን ሲጠይቃቸው*

‘ሴራ እያሴሩ ነው፣ ሴራውን የጠነሰሱት እነማን እንደሆኑ እያወጣን ነው፣ ኢሕአፓ እያንሰራራች ነው?’ የሚል መልስ መስተዋት ትሰጠዋለች።

በዚህ ጊዜ ሁላችንንም በአግርምሞት እየቃኘ ‘የምን ሴራ’ ካለ በኋላ በመቀጠል ‘ምን ታደርጉ የደሃ ልጆች ሁሉ ብርቱካንና ሙዝ እየቀለብናችሁ አምሮባችኋል። አሁንም አርፋችሁ አልቀመጥ አላችሁ’ ብሎ ከደነፋ በኋላ መስተዋትን

‘ሂጂ ጥይት አምጪልኝ ከወዲያኛው ክፍል’ አላት።

ወዲያውኑ ሄዳ አንድ ትንሽ ካርቶን አምጥታ እተቀመጠበት ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠች።

ገራፊዎቹን እየተመለከተ ‘ማነው ሴራውን ያደረገው?’ የሚል ጥያቄ ቢጠይቅ ሁሉም ዝም አሉ። እራሡ እያንዳንዳችንን በየተራ ጥያቄ መጠየቅ ጀመረ።

‘አንተ ምንድነው ያደረከው?’ ‘ማነው ሴራውን የጠነሰሰው?’ ‘ማነው ሴራው ውስጥ ያለበት’ እያለ አንዳንዱን ይጠይቃል። ሁሉም ከሤራው ጋር ምንም እንደማያውቅ ይመልሱለታል።

እኔ ጋ ሲደርስ የጠየቀኝ ጥያቄ

‘አንተን ማነው የጠራህ?’ ብሎ ጥየቀኝ

‘እኔን ማን እንደጠራኝ አላውቅም፤ ተጠርቼ ብቻ መምጣቴን ነው’ የሚል መልስ ሰጠሁት አለፈኝ።

አጠገቤ ጋ ብችሩ የ33 ቀበሌ ነው አጎዛ ገበያ አካባቢ የነበረ ልጅ ትንሽ ፊቱ ላይ ጺም ነበረው ከአሁን በፊትም ያውቀዋል መሰለኝ

‘አንተ ልንይዝህ ቤትህ ስንመጣ ውሻ የለቀክብን አይደለህ እንዴ፣ የኛ ማርክሲስት ብሎ’ ወዲያውኑ በሽጉጥ ሆዱ ላይ ተኩሶ ይመታዋል።

በዚያን ሰዓት አልወደቀም፣ አልተንፈራገጠም። ቀጥ ብሎ ቆሟል። ከአሁን አሁን ይወድቃል ብዬ ስመለከተው ምንም ነገር አልወደቀም። አሁን ወደ ሌላው ቀጠለ ሄድ…ሄድ እያለ አንድ እስረኛ ወደ በሩ አካባቢ የነበረ ልጅ ጋ ሲደርስና ሲጠይቀው ‘ሴራ አይደለም ሴንትራል ኮሚቴው የኢሕአፓ አልታሰረም፣ የተገኘ የለም የሚል ጨዋታ ነው የተጫወትነው። ወሬ’ የሚል ዝምብሎ እንደመጣለት ይመልስለታል። ልጁ ይህንን ያለው የሽጉጥ ተኩስ ስለተሰማ ከመጣ ጭንቀት ይመስለኛል።

በዚያን ጊዜ ‘እነማን ናቸው ይሄንን የተናገሩት? የተነጋገሩት?’ የሚል ጥያቄ ይጠይቀዋል

‘ዳፈማ ያሉ ልጆች ናቸው’ የሚል መልስ መለሰለት። ልጁ ፎቅ ላይ የነበረ ነው ዳፈማ አልነበረም።

አሁን ከፈለኝ ‘ሂድና እነሱን አምጣልኝ’ ብሎ ከደምሴ ጋር ልጁን ላከው።

ቢያንስ ቢያንስ ወደ 16 ሰው የሚሆን ሄደው ይዘው መጡና ‘እነኚህ ናቸው’ ብለው አስረከቡት። ትዝ የሚሉኝ ነገሮች ስማቸውን ባላውቀውም ረጋ ያሉ አስተማሪዎች ሰውነታቸው ተደብድቦ በጣም የተጎዱ ነበሩ። በጣም ከመደብደባቸው የተነሳ እጃቸው ስለማይታዘዝላቸው ብዙ ጊዜ የምናሻቸው እስረኞች ነበሩ።

‘ወደ ምርመራው ክፍል ከገቡ በኋላ ምንም የተጠየቁትም ነገር የለም ብቻ በበሩ በስተቀኝ በኩል ተደረደሩ።

‘ከፈለኝ ከመሃከላችን የነበሩትን ሰዎች በተለይ ጺም ያላቸውንና ረዘም ያሉትን ‘ማርክሲስቶቹ’ በሚል እያፌዘ ወደ እነኚያ በኩል ደባለቃቸው። ከመሃከላችን አንዱን ይወስዳል ሌላውን እየመለሰ መረጣ ያካሂዳል።

‘አሁን አንዱ እየወጣ እየተመለሰ እየተቀነሰ እየተጠራ እየሄደ በአለበት ሰዓት ‘ብርዬ’ የሚል ትዕዛዝ በራሱ ጥሪ እንደተጠራ ትዝ ይለኛል፤

‘ብርዬን አምጡት፣ ጥሩት’ አለ። ብርዬን መርማሪ አካባቢ ያሉ ሰዎች ያውቁታል። እነሱ ጠሩት እና ልክ በሩ ላይ ሲደርስ ተኩስ ተኩሶ በሩ ደፍ ላይ ይጥለዋል። ወደ ጭንቅላቱ አካባቢ ላይ ነው የመታው። ከዚያ በጣም ድንጋጤና ፍርሃት እቤቱ ውስጥ ሰፈነ።


‘በመቀጠል ገና ሲገባ ታስሮ ማዕከል ላይ ይገረፍ የነበረው ግዛው ወሬሳን እንደ ቴክስ ተሸከርክሮ ትከሻው አካባቢ ላይ ተኩሶ መታው። በዚያን ሰዓት በጣም ትዝ የሚለኝ ነገር ልጁ ሕይወቱ ስታልፍ ያደረገው እግሩን እጥፍ ዝርግት በማድረግ ምንም ነገር ሳይንቀሳቀስ ሞተ። ከላዩ የሚፈሰው ደም ግን ከመጠን በላይ ስለነበር በግድግዳው ዙሪያ ተጥለቅልቆ ነበረ።

‘ብርዬ የሚባለው ልጅ ከፈለኝ ጠርቶት ልክ በሩን ከፍቶ ሲገባ በሩ አካባቢ ላይ እንደቆመ ተኩሶ መታውና ተዝለፍልፎ ወደቀ። ብርዬ ወድቆ ነብሱ ሳትወጣ ሰውነቱ በሚንቀጠቀጥበት ሰዓት መስተዋት የምትባለዋ መርማሪ ከከፈለኝ አረመኔው ጠረጴዛ ላይ ቁጭ ያደረገውን ሽጉጥ አንስታ ወደ ብርዬ አፈሙዙን አድርጋ በርከክና ጎንበስ በማለት ‘ከፈለኝ

*ልድገመው…ልድገመው…ልምታው እያለች’ ለመተኮስ የከፈለኝን ምላሽ ትጠባበቅ ነበር። ከፈለኝ ደግሞ ብርዬ ጣር ላይ እንዳለ ስለገባው ‘ተይው እባክሽን’ ሲላት ተመልሳ መምጣቷን አስታውሳለሁ።*

*‘ሁለተኛ ደግሞ ቡችሩ የተባለው የቀበሌ 33 መሰለኝ አጠገቤ ቆሞ ከፈለኝ ተኩሶ ሆዱን ከመታው በኋላ ልብሱን እንደለበሰ ነው የቆመው። በፊት ቀደም ብሎ ለምርመራ የገባ እንደሆነ ልብሱን አለማውለቁ ይመሰክራል። ማለትም በኋላ የምንገባውን ነበረ ልብስ አውልቁ የሚሉት።*

*‘ከፈለኝ እንደገባ ጺም ስለነበረው ተኩሶ ሆዱን ከመታው በኋላ መሃል ላይ ከፈለኝ እየጠየቀን ከቆየ በኋላ ‘ከፈለኝ…ከፈለኝ ሀኪም ቤት ውሰደኝ እድናለሁ’ ብሎ ይለማመጠውና ይለምነው ነበረ። በዚያ ሰዓት ከፈለኝ የመለሰለት መልስ ‘ዝምበል የደሃ ልጅ ትረሸናለህ’ የሚል ቃል ነበር። በኋላም ከሌሎች ጋር ተደባልቆ ተገደለ። (ሥዕል 13)*



ሥዕል 13. አድማ/ሜራ ተብሎ የተደረገው ግድያ ነፀብራቅ

*‘በመቀጠል ቀደም ሲል የመረጣቸውን ሰዎች ‘በገመድ እሰርልኝ’ የሚል ትዕዛዝ አስተላለፈ።*

*‘ደምሴና ጃምቦ የሚባሉት መርማሪዎች በጥድፊያ እዚያው አካባቢ አለ ግንድ ላይ ገመድ በቆንጨራ ቆራርጠው ተጠርተው የመጡትንና ከእኛም መሀል ጺም ስላላቸው ብቻ የተመረጡትን ወደ 14 የሚደርሱ ልጆች እጃቸውን ወደ ኋላ የፊጥኝ አሰሯቸው። አሁን እንግዲህ ሦስት ሰዎች እዚሁ ምርመራው ክፍል ውስጥ በጥይት ተገድለዋል።*

*‘ዮናታን እራሱን ስቶ ሰብሮ በወጣው መስኮት በኩል የራሺያ ካፖርት የለበሰ አብዮት ጠባቂ በሁኔታው በጣም በመገረም ይቁነጠነጥ ነበረ። እልህም ውስጥ ያለ ይመስል ነበረ። እልሁ ፊቱላይ ይታይበት ነበረ። ከውጭ ሆኖ ፊት ለፊት ብርሃን እላዩ ላይ ስለሚያበራ ንዴቱ በተቆጨ ስሜት ይታይበት ነበረ።*

*‘የታሰሩትን ወጣቶች በሰልፍ ይዘዋቸው ወጡ። ልክ ከተወሰነ ሰዓት በኋላ የተኩስ እሩምታ ከግቢው ወጣ ብሎ ይሰማ ነበረ። ተኩሱ በጣም…በጣም…በጣም…አንድ ትልቅ ጦርነት የሚካሄድበት አውድማ ይመስል ነበር። የፍራት ዱላ ይመስላል። በጣም ብዙ ድምጾች ሲጯጯሁ ይሰማል። የሰቆቃ ድምጽ።*

*‘ከዚያ ከተወሰነ ሰዓት በኋላ ይመለሳሉ። በሚመለሱበት ሰዓት እነ ከፈለኝ በመጀመሪያ የነበራቸው ‘ግርማ ሞገስ’ ‘ትልቅነት’ ጠፍቶ እጃቸው እየተንቀጠቀጠ እዛች እነበረበት ጠረጴዛ ላይ ቁጭ አለ። ገድሎ መጥቶ እጁ የመንቀጥቀጥና የፍርሃት ባህሪዎች ይታዩበት ነበር። ከዚያ ‘እነኚህን ደግሞ ለነገ መዝግብና አሳድራቸው። እነኚህን ነገ እንረሽናቸዋለን’ የሚል ትዕዛዝ ሰጠ።*

*‘አሁን ያንን ከተናገረ በኋላ ትዝ የሚለኝ ዙሪያውን ቆመን የነበርነውን “ቁጭ በሉ” አለን። እዚያው ውስጥ በጥይት ከተመቱት ልጆች ሬሳዎች የፈሰሰው ደማቸው ዙሪያውን ወለሉን አጥለቅልቆት ስለነበረ ቁጢጥ በምንልበት ሰዓት*

*‘ቁጭ በሉ ደሙ ላይ ቁጭ በሉ የወንድሞቻችሁ ደም ነው ይቀፋችኋል እንዴ?’ የሚል ንግግር ተናገረ።  ቀጠለና ክፍሉ ውስጥ በጥይት ተመተው የወደቁትን የልጆቹን ሬሳ ‘አንሱና ውሰዱ’ ብሎ ትዕዛዝ ለኛ ለቀረነው ሲነግረን ሁላችንም ዝም ብለን ቁጭ ስንል ‘እነኚህ ደብሯቸዋል ተዋቸው ከአዳራሹ ሌሎች ልጆች አምጡና አስጭኑ’ አለ። የአሸዋ መጫኛ ባሬላ አምጥተው እሱላይ ለመጫን ሲታገሉና በዚያ እንደወጣ ሁሉ ትዝ ይለኛል። የሬሳው  አያያዙና የአጫጫኑ ሁኔታ በጣም የሚያሳዝን ነበር። ሟቾቹን በባሬላ ከግራና ከቀኝ ይዘው ቀደም ሲል አውጥተው ደጅ ተረሸናቸው ጋር ደባለቋቸው።*

*‘ከዚያ ስማችንን ተመዘገብን። እሱም ሌሎቹም ድንጋጤ ነበራቸው የሚናገርም መርማሪ የለ። እነ ደምሴና ጃምቦ ምንም ዓይነት ንግግር አልነበራቸውም ፀጥ ያለ ነበር።*

*‘ልብሳችንን ያወለቅነው ያዝን “ሂዱ ውጡ” ብሎ ትዕዛዝ ሲሰጠን። ለዕውነት ከሆነ ከሰባት እስከ አሥር እንሆናለን የተመለስነው አንድ በር በተራ መውጣት አቅቶን በግፊያ ያቺ በር እንደጠበበችን ትዝ ይለኛል። ከድንጋጤ የተነሳ ልብሳችንንም ለመልበስ ዕድል አላገኘንምና በእጃችን እንደያዝን ተፈተለክን።*

*‘ሰዓቱ ከምሽቱ አምስት ሰዓት አካባቢ ይሆናል ዱላውና ግርፉ በጣም…በጣም ስለበዛ እና እረዥም ጊዜ ምርመራው ክፍል ውስጥ ስለነበርኩኝ መውጫው አካባቢ የነበረችውን ውኃ እዚያው አካባቢ ያገኘሁትን የምግብ ሰሀን አጠብኩኝና እራቁቴን ውኃ ጠምቶኝ ስለነበረ ሳህኑን ሞልቼ እየጠጣሁ ሳለ ያ በመስኮት ያየን የነበረ አብዮት ጠባቂ በንዴት*

*‘ምን ሆናችሁ ነው? ምን አድርጋችሁ ነው?’ የሚል ቃል በጣም በሁኔታው በመቆጨት ይናገረኝ ነበረ።*
*‘አይ ምንም የምናውቀው ነገር አልነበረም፣ ምንም የሠራነው ነገር የለም፣ አሁንም ምንም የማውቀው ነገር የለም’ ብዬ ስነግረው*
*‘እናንተም አታርፉም ምናለ ለቤተሰቦቻችሁ እንኳ ብትተርፉላቸው’ የሚል የቁጭት ቃል ተናገረኝና እኔም ተነስቼ ወደ ክፍሌ ሄድኩኝ።*

*‘ወደ መኝታ ክፍል ስሄድ ቢያንስ ቢያንስ በእስር ቤቱ ውስጥ የነበረው ከ1500 ሰው በላይ ነበረ። ነገር ግን አንድ ድምጽ፣ አንድ ኮሽታ፣ አንድ የሳል ድምጽ እንኳ አይሰማም ነበር። ጭለማ ውስጥ በዳፈና ስለማይታይ እየተደናበርኩ ‘አድፍጠው’ በተኙት ሰዎች ላይ እግራቸውን እየረጋገጥኩ እላያቸው ላይ እየወደቅሁ ስራመድ ረገጥከን፣ ወደክብኝ የሚል አንድ ቃል አልነበረም። እኔ የነበርኩት ዳፈማ የመጨረሻው መስኮቷ አካባቢ ስለነበረ አቋርጬ በምሄድበት ሰዓት ምንም ዓይነት…ምንም ዓይነት የድምጽ መልስ አልነበረም።*

*‘እዚያ ደረስኩኝ አብረውኝ የነበሩ እነ ንጉሤ ሚባሉ*
*‘ምንድነው?’ ብለው ሲጠይቁኝ*
*‘ተዉኝ አሁን ልተኛበት’ ብዬ ተኛሁ።*

*ከትንሽ ደቂቃ በኋላ የከባድ ትራክ መኪና ድምጽ ተሰማ። ወዲያውኑ እሬሳው ሲጫን ጓ! ጓ! የሚል ድምጽ ረጭ ያለውን ፀጥታ ሰብሮ ይሰማኝ ነበር። ይህንን ከሰማሁ በኋላ በግቢው ውስጥ አንድ ኮሽታ፣ አንድም ድምጽ ሳይሰማ እኔም እንቅልፍ ወሰደኝ። በጣም…በጣም ደክሞኝ ስለነበረ ሲነጋ ሁሉ አልታወቀኝም ነበር።*

*'ጊዜው ረዥም ስለነበረ በመሃከሉ አንዳንድ ነገሮችን ልዘነጋ እችላለሁኝ። ስሞች ከሞላ ጎደል በግድያው የተካፈሉት ሰዎች ደምሴ፣ ሻንቁ፣ ጃምቦ፣ አስናቀ፣ ከፈለኝ፣ መስተዋት ነበሩ።*

*'የዚያች ቀን ሁኔታዎች የሚገርማችሁ ነገር ፊት ለፊት አሁን ከ36 ዓመት አካባቢ ሆነው እንደ ፊልም ሁሉም ቁልጭ ብለው ጭንቅላቴ ውስጥ አለ ሊሠርዝ አልቻለም። ይሄ ነው ከሞላ ጎደል የነበረው ሁኔታ። የቀረ ሊኖር ይችላል። አመሰግናለሁ።"*

**<u>የከፍተኛ 15 ቀበሌ 32ቷ አበበች ደምሴ፡-</u>** *"በከፍተኛ 15 እስር ቤት በነበርኩበት ወቅት ትዝ ከሚሉኝ አንዱ 'አድማው' ነው። ቀኑ የካቲት 4 ነው በማላውቀው ምክንያት ምርመራው ክፍል ተጠራሁ። ስገባ እነ መስተዋት፣ ሱራፌል፣ ደምሴ፣ ጃምቦና እህቱ ሻንቄ፣ አስናቀ እስረኛውን ይደበድባሉ፣ ይገርፋሉ። ምርመራው ክፍል ስገባ ግዛው ወሬሳ ታስሮ ይደበደባል። እኔንም አስገብተው ልብሴን አስውልቀው በውስጥ ሱሪ ብቻ ከሌሎች ጋር ቆምሁ። በወቅቱ የነበርኩት ሴት እኔ ስሆን እንደ እኔ በውስጥ ሱሪ ብቻ ያሉ በርካታዎች አሉ። በዚህ ሁኔታ እያለን ነው ከፈለኝ የመጣው። እመግረፊያው ክፍል ታስሮ ሲገረፍ የነበረውን ግዛውን ሲገድለው እዚያው ነበርኩ። የኛን ቀበሌ ብቹሩንም ሆዱ ላይ ከመታው በኋላ 'ጋሽ ከፈለኝ ለእናቴ አንድ ነኝ። ወደ ሆስፒታል አስወስደኝ፤ ሐኪም ቤት ብሄድ እድናለሁ' እያለ ሲለምነው፤ ከፈለኝ የለበጣ ሳቅ እየሳቀ አስተያየቱ ሁሉ ትዝ ይለኛል። በመቀጠልም እኔንና ሌላ ልጅ 'ሁለታችሁን በአንድ ጥይት ነው የምገድለው፤ ጥይት አላባክንም' ብሎ አነጣጥሮ የተኮሰው ጥይት እኔ አጭር በመሆኔ እኔን ስቶ ልጁን ሊመታ ችሏል። በመጨረሻም ካለነው ውስጥ እየመረጠ ወደ 16 ልጆች አውጥቶ ሲገድል እኔ በአጋጣሚ ልተርፍ ችያለሁ።*

*'በማግስቱም የተገደሉትን ልጆች ስም ጽፈሽ አምጪ ተብዬ ጽፌ ሰጥቻለሁ። ከማስታውሰው ውስጥ በዛ ገ/ሕይወትን የገደለበት ምክንያት ቀን የበዛን ምሳ ከፈለኝ ወስዶ ሲበላ 'ከፈለኝ ለምን ትበላብኛለህ ምሳዬ እኮ ነው' ሲለው የተረፈውን ሲመልስለት 'ይህ የመጨረሻ ምግብህ ይሆናል' በማለት ነበር የዚያ ለት ማታም አውጥቶ ገደለው። አሸናፊ ደግሞ ላዳ መኪና ስለነበረው እሱን ለመውሰድ ሲል ነው የገደለው።"*

**<u>የከፍተኛ 15 ቀበሌ 27ቱ ታከለ ሰይፉ፡-</u>** *"ልክ የካቲት 4 ቀን ነው የተያዝኩት። ከኢ.አ.ዩ. የያዘኝ በላይ ሳሙኤል ከግርማ ኮሚኒስት ጋር በአስናቀ ጠቋሚነት ነው። መምህር አብዱ ከሌላ ቦታ ይዘውት አብረን ነው የገባን። ወደ ተሰዓት ላይ ታስሬ መገረፍ ጀመርሁ። እነ ሱራፌልና ደምሴ ሲገርፉኝ የቀይ ሽብር ኮሚቴ አባሉ አሳምነው ጠረጴዛው ላይ ቁጭ ብሎ ምርመራውን ይመራል። ወደ አንድ ሰዓት ገደማ እየተደበደብኩ እያለሁ አድማ ሴራ እያደረጉ ነው ሲባል እነማናቸው አምጧቸው እየተባለ ሲሯሯጡ ዱላው ቀረልኝ። አሳምነው አስፈታኝና ቀደም ሲል ከተገረፈው ከመምህር አብዱ ጋር ምርመራው ክፍል ውስጥ ወደ ጥግ ተቀመጥን። ይደረግ የነበረውን ግርግር ሁሉ እመለከት ነበር። የተወሰኑትን እያንጋጉ ያመጣሉ ይገርፋሉ። ደግሞ ሌሎች ይተካሉ። በዚህ ሂደት ከፈለኝ ሞቅ ብሎት ይመጣል። ግዛውንና ኃይሉ ታደሰን እዚያው ምርመራ ክፍል ተኩሶ ሲመታቸው አይ ነበር። ኃይሉን ሆዱ ላይ መትቶት በኋላ ሲንፈራፈር አይቶ ከተማ ይመስለኛል 'ይህ ደግሞ ምንድነው የሚያንፈራፍረው' ሲል 'ተወው በሆዱ ጥይት ይዞ ነው። እንጨርሰዋለን' ሲል ከፈለኝ አስታውሳለሁ።*

*'በጣም ስለተገረፍኩኝ ከንፈሬ ደርቆ ነበርና በምላሴ ላብስ ከንፈሬን ነከስ…ነከስ ሳደርግ የቀበሌ 32 ይመስለኛል ተረፈ 'ኧረ ከንፈሩን ይነክሳል' ብሎ ሲጮህ ከፈለኝ ወደኔ በፍጥነት ዞረና 'የቱ ነው' በማለት ሽጉጡን ደቀነብኝ። ወዲያው አሳምነው ሁኔታውን ይከታተል ነበርና 'እንዳትነካው ምርመራውን አልጨረሰም ገና ይቀረዋል' ሲለው መለስ አለ። ወደ ከፍተኛ 15 እሥር ቤት የገባሁበትን የመጀመሪያ ቀን በዚህ ሁኔታ አስታውሰዋለሁ።"*

**<u>የከፍተኛ 15 ቀበሌ 23 ግርማ ክፍለመስቀል፡-</u>** *'የአድማው መነሻ ዋናው 'አደሙ ስኳርና ሚፈልጉትን ደበቁ' ነው። ሌላው ከበበውም ብሎታል የሚወራው እኛም በየክፍሉ እናወራው ነበር 'የወጣቱ መዋቅር ተመቷል፤ የፓርቲው ይኖራል' እያልን። ዝም ብለን የምንለው ነበር። ተኩስና ድንጋጤው አንዳንዱ ይኼን አውርቻለሁ ማለት ጀመረ። በዚህም እነ ከፈለኝ ግድያቸውን ሕጋዊ አደረጉት። 'አደሙ፣ ኢሕአፓ እያንሰራራች ነው' አለች ያቺ መስተዋት። በአንድ ምሽት ወደ 18 ልጆች ከፈለኝ አድማ ብሎ ገደለ ሌላ የሚገርመው ከሚመረምሩት ውስጥ አንዷ ያቺ ቆንጆዋ እስረኛዋ እሞቱት ልጆች ላይ ቼካፕ ታደርግ ነበር።*

**<u>የከፍተኛ 15 ቀበሌ 26ቱ አክሊለማርያም፡-</u>** *“በወቅቱ የ13 ዓመት ልጅ ነበርኩኝ። ታላላቅ ወንድሞቼ በቤት ውስጥ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ እከታተላለሁ። በቀይ ሽብር ዘመን ሁለቱም ወንድሞቼ ከፍተኛ 15 ታስረዋል። እኔንና በእኔ ዕድሜ ክልል ያለን ሕፃናትን ማጋለጥ አሉና ሰብስበው ቀበሌ አጎሩን። ወደ ሃምሳ እንሆናለን። እነኚህ የቀበሌዎቹ ከፍተኛ እሥር ቤት እንደሚያሰቃዩት አለቆቻቸው እነሱ ደግሞ ወጣት ሁሉ ስለታሰረባቸው እኛ ሕፃናቶችን በማሰቃየት አብዮቱን ሊገነቡ ፈለጉ። ቀበሌ አሠሩንና በሳምንቱ የካቲት 3 ቀን 1970 ዓ.ም. አምስት የምንሆን ከፍተኛ 15 አመጡን። ከፍተኛ 15 ታስሮ የነበረው የኃይሉ ታደሰ ሁለት ታናናሽ ወንድሞቹ ተሾመና ዳዊት (የ11 ዓመት ታዳጊ) አብረውኝ ታስረዋል። ዘ ኬቨ እሚባለው በርካታ እሥረኛ አለበት ውስጥ ከተቱኝ። በማግስቱ እደጅ ፀሐይ ስንሞቅ ብርዬ ‘ወንድምህ መጥቷል’ ብለው ስለነገሩት ሊያየኝ መጣ። ‘አለህበት ወይ?’ ብሎ ጠየቀኝ። ‘አዎ’ አልኩት። ‘አይዞህ’ ብሎና አበረታቶኝ ወደ ክፍሉ ሄደ። የዛኑ ዕለት ማታ ወንድሜን ብርዬን ገደሉት። ምን ሊሰማኝ እንደሚችል ቋንቋ የለኝም። ብቻ ይታያችሁ። ኃይሉ ታደሰም አብሮ ተገድሏል። ለካ የገባሁ ማግስት ነው አድማ/ሜራ የተባለውና የገደሏቸው።*

*‘ወንድሜ ብርዬ ከፍተኛ 15 እሥር ቤት ከመከፈቱ በፊት ከገራፊው ደምሴ ጋር ተይዘው ስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ነበሩ። ከፍተኛ 15 እሥር ቤት ሲከፈት ሁለቱንም ወሰዷቸው። ወንድሜ ዝቅተኛ ቦታ እንደሆነ አድርጐ ሲቀመጥ ደምሴ ተገልብጦ እሥር ቤቱ ውስጥ ገራፊ ሆነ።*
*‘የአድማው እለት የማስታውሰው ብርዬ መጀመሪያ ጠርተውት ወሰዱትና ሲመለስ ደምሴ ገራፊው ፎቁ ላይ ያገኘውና ‘ለምንድነው የምትመለሰው?’ ሲለው ‘ሂድ ብለውኝ ነው’ ብሎ ሲመልስለት ይሰማኛል። የዛ ዕለት ደምሴ የብርዬን ጃኬት ነው የለበሰው። ከብርዬ ጋር አብረው የሚሠሩ ይመስለኛል እቤት ሲመጣ አየዋለሁ። እንደምገምተው ብርዬ ከደምሴ ጋር የሠሩት ሥራ አለ። ደምሴ ብርዬ ይህንን ሚስጥር እንዳያወጣበት ይህ አድማ የተባለ ግርግር ጠቅሞት ወንድሜን እንደገና አስጠርቶት ይዞት ሄደ። ተገደለ።*

*‘ብርዬ በኢሕአፓ እንቅስቃሴ እጅግ ጠንካራ ነበር። ቤታችን የሚባዙ ወረቀቶች፣ ቀለም ሁሌ አያለሁ። ወደ ማታ እየመጡ ለሊቱን ሲሠሩ ነው የሚያድሩት። ከቤታችን አጠገብ ሒልተን ሆቴል ጀርባ እግር ኳስ የምንጫወትበት ሜዳ አለ። ብርዬ የሠፈር ወጣቶችንና ሕፃናትን እየሰበሰበ እሜዳው ላይ ፊልም ያሳይ ነበር። ፊልሙ በአብዛኛው የድሮ የቬትናም፣ የቻይናና የራሺያ አብዮትን የሚመለከቱ ነበሩ። በተለያየ ቀን ያሳዩ ነበር። ይህም ሁኔታ ብርዬን በቀበሌው ተመራጮች ጥርስ ውስጥ እንዲገባ አድርጐታል።*

*‘ብርዬንም ገደሉት እኔም ታላቅ ወንድሜም ተፈታን። ለአለፉት 33 ዓመት ገደማ ለአንድ ቀን አውርተን አንስተን አናውቅም። እቤትም እናቴም ሆነች ሌሎቻችን በውስጣችን ስንብሰለሰል ነው የኖርነው። እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ለስብሰባ ወጥቼ ስለ ከፍተኛው እሥር ቤት ያወራሁት የወ/ሮ ቆንጂት መጽሐፍ “ምርኮኛ” የወጣ ጊዜ ነው።*

*‘ከወንድሜ መገደል ሌላ በልጅነት ዕድሜዬ እንደ ወንድሜ ትዝ የሚለኝ ነሲቡ ነው። በየቀኑ እየተሸከሙ ሲወስዱት ቀጥቅጠው ሲመልሱት አያለሁ። ያሳዝነኛል እጅግ ውስጤ የተቀረጸ ልጅ ነበር። ከቀይ ሽብር ዘመን በኋላ አይቼው አላውቅም። እዚህ በዲሲ የወ/ሮ ቆንጂት “ምርኮኛ” መጽሐፍ ምረቃ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰው በተሰበሰበበት ወጣሁ። ስለ ነሲቡ ሳወራ የሚያውቁት አገኘሁና ወዲያው በስልክ አገናኙን። ተላቀስን።*

*‘እግዚሃብሔር ይስጠው ይኸው ዛሬ ብቻውን ማለት እችላለሁ በሚያደርገው ልፋትና ጥረት እኔንና እኔን መሰሎች አሰባስቦን የወደቁ ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን ስም ከፍ እያደረግን ነው። ወንድሜን በ«ያ ትውልድ ተቋም» ድረ ገጽ አገኘሁት፣ እጅግ ደስ ብሎኛል። አሁን ስለዚያ ጭለማ ዘመን በደንብ አወራለሁ። ለአሁኑና ለመጪው ትውልድ ካላወራነውና ካልጻፍነው የምንጐዳው እራሳችንን ነውና አሁን እየሠራን ባለነው የዚያን ትውልድ ታሪክ ማሰባሰብ በጣሙን ደስተኛ ነኝ።”*

በዚህ ሁኔታ የካቲት 4 ቀን 1970 ዓ.ም. በአንድ ምሽት ከፈለኝ ብቻውን ከቀይ ሽብር ኮሚቴ አባላት ውጭ ወደ 18 ልጆች ገደለ። ምሽቱ በግቢው ውስጥ ሁካታና የጥይት ሩምታ እንደተሰማ የሰቆቃው ለሊት ተራውን ለቀኑ ለቀቀ። በማግስቱ ሁሉም እስረኛ ምን እንደተፈጠረ ግራ እንደገባው ያስታውቃል። ጠዋት በለሊት ሁሉም መጸዳዳት ፈልጎ ሰልፉ ከወትሮው በተለየ እረዝሟል። ከወደላይ ዘአማንኤል የለሊቱን አድማ/ሜራ ተብሎ ግድያ ሰምቶ እየተወራጨ ሲመጣ ብዛት ያለው እስረኛ ለመጸዳጃ ተሰልፎ ያያል “ምድረ ዲሞ በየክፍልሽ” ብሎ ሁለት ጊዜ አከታትሎ ወደ ሰማይ ሲተኩስ ሁሉም እየተተራመሰ የነብስ አውጪን ወደ አለበት ክፍል ከመቅጽበት እየበረረ ገባ። ቀኑን ሁሉም እክፍሉ ተቀምጦ እየተንሾካሾከ ዋለ።

ቤተሰብ የለሊቱን ተኩስ ሰምቶ በለሊት እደጅ ፈሷል። እነማን እንደተገደሉ በደንብ ስላልታወቀም በዕለቱ ለማንም ቤተሰብ ሳይነገር ከተጣራ በኋላ ነው በሌላ ቀን የተገደሉት ልጆች ልብስ የተመለሰላቸው። ምንም በሌለ አድማ በከፍተኛ 15 ውስጥ ለየት ያለና ዘግናኝ ግድያ በነመስተዋት፣ ደምሴና ሱራፌል ጠንሳሽነት በከፈለኝ ገዳይነት ተካሄደ።

ማምሻውን ዘአማንኤል ሰክሮ መጥቶ ተራውን የተወሰኑ ቁጥር ያላቸው ከአሥር በላይ እስረኞች ከየክፍሉ መርጦ አስወጣ። ከሰርቪስ ቤቶቹ ጋራዥ ፊት ለፊትና በጅምር ካለው ሕንፃ በስተቀኝ ያለው ባዶ ቦታ ብዙ ጊዜ ስብሰባ ሲደረግ የምንወጣበት ነው። እዚያ ቦታ ላይ ከየክፍሉ ያወጣቸውን ወንዶችና ሴቶች በጭለማው አንበርክኮ ያስለፈልፋል።

“ምንድነው ያደረጋችሁት አድማ አውጡ” እያለ ሽጉጡን ደግኖ እላያቸው ላይ ይጮኃል። ግማሹ ያለቅሳል፣ አንዳንዱ በልመና ቃና “ኧረ ምንም ምናውቀው የለም” ድምጽ ያሰማል። ከወጡት ውስጥ ቶማስ ቲያትረኛው አንዱ ነው። ድምጹ ለየት ስላለ ይሰማናል።
“ጋሽ ዘአማንኤልዬ ምንም ምናውቀው የለም፣ ጋሽ ዘአማንኤልዬ ምንም ያደረግነው ነገር የለም” እያለ ይለምናል፣ ይማጸናል። በስካር ድምጽና ሁኔታ እየተንተባተበ
“አውጣ ጭንቅላትህን ሳልለው” ይላል ይፎክራል።
ሌላ የሴት ድምጽ ይሰማል ”ጋሽ ዘአማንኤልዬ ለእናቴ አንድ ነኝ ምንም አላውቅም፣ ምንም አላደረኩም”።
ይጨፍራል ዘአማንኤል “አውጪ ተናገሪ ያደረጋችሁትን ምድረ ዴሞ ሁሉ” ለፈለፈ አስለፈለፈ።
በየመሃሉ “ቁጭ በይ ቀና እንዳትል አለቀልህ” የማይለው የለም። መጨረሻም ላይ አከታትሎ ሦስት አራቴ ተኮሰ እረጭ አለ። ድምጽም የለም።

“የተረፈ አለ? የተረፈ አለ? ቀና በል” ይላል ዛማንኤል። መልስ የሚሰጥም የለ። ጥሏቸው ይሄዳል። ሁሉም ቀስ እያለ እራሱን ሲዳብስ አልተመቱም። በአናታቸው ላይ ዝም ብሎ ነው የተኮሰው። ማን ደፋር ከወደቀበት ይነሳ። ትንሽ ቆይቶ እነ ደምሴ መጥተው እተደፉበት በጉማሬ እየደበደቡ “ተነስ ተነስ ወደ ክፍል” እያሉ ያገኙትን እየገረፉ የወደቁትም በደመነፍስ እየበረሩ ወደ አሉበት ክፍል በጨለማው እየተደናበሩ ገቡ።

**የያ ትውልድ ታሪክ ህያው ነው!!!**

**ያ ትውልድ ተቋም ለመረጃ ምንጭነት!!!**

**ያ ትውልድ ተቋም**

**የካቲት** 04 **ቀን** 2015 **ዓ.ም.** (February 11, 2023)

Email : yatewlid@gmail.com 7033004302 USA
website : http://www.yatewlid.com, http://www.yatewlid.org

Facebook:- Yatewlid The Generation